ሚያዝያ 13 ቀን 2007 ዓ.ም

# የሀዘን መግለጫ መልእክት

በሊቢያ ISIS በተባለ የሽብርተኛ ቡድን በግፍ የተገደሉ ዜጎቻችን ሞት ከተሰማበት ሰዓት ጀምሮ መላው የአገራችን ሕዝብና መንግሥት በጥልቅ ሃዘን ውስጥ ይገኛል፡፡ ይህንን የግፍ ግድያ በተመለከተ የወጡትን መረጃዎች መነሻ በማድረግ መንግሥት የሟቾቹን ማንነት ለመለየት ባደረገው የማጣራት ስራ ዜጎቻችን መሆናቸውን ካረጋገጠ በኋላ የተሰማውን ከፍተኛ ሃዘን አስመልክቶ መግለጫ አውጥቷል፡፡ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትራችን አቶ ሃይለማርያም ደሳለኝ በሽብርተኛ ቡድኑ ለተገደሉ ዜጎቻችን የተሰማቸውን ጥልቅ ሃዘን ገልጸው ለሟች ቤተሰቦችና ለመላው የአገራችን ሕዝብ መጽናናትን በመመኘት፣ በሽብርተኛ ቡድኑ የተፈጸመው ኢ-ሰብዓዊና አረመኔያዊ ድርጊት በማውገዝ አገራችን የፀረ ሽብር ትግሉን አጠናክራ እንደምትቀጥል ገልጸዋል፡፡

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በጠራው አስቸኳይ ስብሰባ በሊቢያና በደቡብ አፍሪካ በሚገኙ ዜጎቻችን ላይ በደረሰው የግፍ ግድያ የተሰማውን መሪር ሃዘን የገለጸ ሲሆን፣ የሽብርተኛ ቡድኑንም ድርጊት አውግዟል፡፡ ምክር ቤቱ ከሚያዝያ 14 ቀን ጀምሮ ለሦስት ተከታታይ ቀናት ብሔራዊ የሃዘን ቀን እንዲሆን ያወጀ ሲሆን፣ ይህም በሁሉም የኢትዮጵያ ክልሎች፣ በሁለቱም የከተማ አስተዳደሮች እንዲሁም በውጭ አገር በሚገኙ የኢትዮጵያ ኤምባሲዎች፣ የቆንስላ ጽ/ቤቶች፣ የንግድ ጽ/ቤቶች እና የኢትዮጵያ መርከቦች ሰንደቅ ዓላማችን ዝቅ ብሎ እንዲውለበለብ ወስኗል፡፡

ኤምባሲያችንም በሊቢያና በደቡብ አፍሪካ በግፍ የተገደሉ ዜጎቻችን ሞት ላይ የተሰማውን ጥልቅ ሃዘን እየገለጸ፣ በሽብርተኛ ቡድኑ የተደረገውን እኩይ ተግባር በፅኑ ያወግዛል፡፡ በተጨማሪም ኤምባሲያችን በሚሸፍናቸው በኖርዲክ አገሮች የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን፣ ትውልደ ኢትዮጵያውያን እንዲሁም የኢትዮጵያ ወዳጆች በሙሉ ይህንን እኩይ ተግባር በማውገዝ ኮሚኒቲው በሚሰባሰብባቸው በተለያዩ የእምነት ተቋማት በመገናኘት በጥቃቱ ሰለባ ለሆኑት ዜጎቻችን የመታሰቢያና የፀሎት ስነስርዓት እንዲያካሂዱ እንዲሁም የተለያዩ አማራጮችን በመጠቀም ድርጊቱን አጥብቀው እንዲያወግዙና ሃዘናቸውን እንዲገልጹ ጥሪውን ያስተላልፋል፡፡ ኤምባሲያችን በዜጎቻችን ላይ የደረሰውን ጥቃት በማውገዝ የጥቃቱ ሰለባ ለሆኑት ዜጎቻችን የመታሰቢያና የፀሎት ስነስርዓት በስቶክሆልም የሚያዘጋጅ መሆኑን እየገለፅን ቦታውንና ቀኑን በተቻለ ፍጥነት የምናሳውቅ መሆኑን እንገልፃለን፡፡ በተጨማሪም ከሀሙስ ሚያዝያ 15 ቀን ጀምሮ በፅ/ቤታችን የህዝብ የሀዘን መግለጫ መዝገብ የምናዘጋጅ መሆኑን እናሳዉቃለን፡፡

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ኤምባሲ

ስቶክሆልም